ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሀያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፰
አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፪

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.78
ADDIS ABABA, Sepetember 2nd 2020

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፸፬/፪ሺ፲፪
የኢንቨስትመንት ደንብ ገጽ ............................፲፪ሺ፯፻፷፩

Content

Regulation No. 474/2020
Investment Regulation Page............................12761

ደንብ ቁጥር ፬፻፸፬/፪ሺ፲፪

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢንቨስትመንት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹/፪ሺ፲፪ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር ፬፻፸፬/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

REGULATION NO. 474/2020

COUNCIL OF MINISTERS INVESTMENT REGULATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers of the Federal Democratic Republic of Ethiopia pursuant to Article 55 Sub-Article (1) of the Investment Proclamation No. 1180/2020.

PART ONE

GENERAL

1. **Short Title**

   This Regulation may be cited as the "Investment Regulation No. 474/2020".

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡

፩/ "አዋጅ" ማለት የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹/፪ሺ፲፪ ነው፡

፪/ በዚህ ደንብ ውስጥ ያሉ ሌሎች ቃላት እና ሐረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

**ክፍል ሁለት**

**የኢንቨስትመንት መስኮች**

**፫.ከመንግሥት ጋር በቅንጅት የሚከናወኑ ኢንቨስትመንቶች**

ማንኛውም ባለሀብት በሚከተሉት የኢንቨስትመንት መስኮች መሠማራት የሚችለው ከመንግሥት ጋር በቅንጅት ብቻ ይሆናል፡

፩/ የጦር መሳሪያዎችን፣ ጥይቶችን እና ለጦር መሳሪያነት የሚሆኑ ወይም የጦር መሳሪያ ለመሥራት የሚያገለግሉ ፈንጂዎችን ማምረት፡

፪/ የኤሌክትሪክ ኃይል ወደ አገር ውስጥ ማስገባት እና ወደ ውጭ መላክ፡

፫/ ዓለምአቀፍ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት፤

፬/ ፈጣን የመንገድ ትራንስፖርት፡ እና

፭/ ፈጣን የፖስታ አገልግሎትን ሳይጨምር የፖስታ አገልግሎት።



**2. Definitions**

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "Proclamation" means the Investment Proclamation No. 1180/2020;

2/ Other words and phrases in this Regulation shall have the definition assigned to them in the Proclamation.

**PART TWO**

**INVESTMENT AREAS**

**3. Investment Areas Reserved for Joint Investment with the Government**

Any investor may invest in the following investment areas only jointly with the Government.

1/ Manufacturing of weapons, ammunition and explosives used as weapons or to make weapons;

2/ Import and export of electrical energy;

3/ International air transport services.

4/ Bus rapid transit; and

5/ Postal services excluding courier services.

**፬. ለአገር ውስጥ ባለሀብት የተከለሉ የኢንቨስትመንት መስኮች**

የሚከተሉት የኢንቨስትመንት መስኮች በአገር ውስጥ ባለሀብት ብቻ የሚካሄዱ ይሆናሉ፣

፩/ አግባብነት ባለው ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ እና የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ሥራን ሳይጨምር፡ የባንክ፣ የኢንሹራንስ፣ እና አነስተኛ የፋይናንስ ሥራዎች፣

፪/ በተያያዙ የብሔራዊ ዋና-ዋና መስመሮች የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፍ እና ማከፋፈል፡

፫/ የመጀመሪያ እና መካከለኛ የህክምና አገልግሎቶች፡

፬/ ነዳጅ እና የነዳጅ ምርቶችን ማቅረብ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የተመረተን የራስ ምርት በጅምላ መሸጥ፣ እና ኤሌክትሮኒክ ንግድን ሳይጨምር የጅምላ ንግድ፡

፭/ አግባብነት ባለው ሕግ በተደነገገው መሠረት ኢትዮጵያ ውስጥ የተመረተን የራስ ምርት በችርቻሮ መሸጥን እና ኤሌክትሮኒክ ንግድን ሳይጨምር የችርቻሮ ንግድ፡

፮/ ቡታጋዝ እና ቢቱመንን ሳይጨምር የገቢ ንግድ፡

፯/ ጥሬ ቡና፣ ጫት፣ የቅባት እህል፣ ጥራጥሬ፣ ማዕድናት፣ ቆዳ እና ሌጦ፣ የተፈጥሮ ደን ውጤቶች፣ ዶሮ፣ እና የጋማ-ከብቶችን ጨምሮ ከብቶችን ከገበያ በመግዛት የመላክ ወጪ ንግድ፡

፰/ ከደረጃ ፩ በታች የሆነ የኮንስትራክሽን እና የቁፋሮ አገልግሎት፡

፱/ የኮከብ ደረጃ ያላቸውን ሳይጨምር የሆቴል፣ የሎጅ፣ የሪዞርት፣ የሞቴል፣ የእንግዳ ማረፊያ እና የፔንስዮን አገልግሎቶች፡

፲/ የውጭ አገር ብሔራዊ ምግብ የሚያቀርብ የኮከብ ደረጃ ያለው የሬስቶራንት አገልግሎትን ሳይጨምር የሬስቶራንት፣ የሻይ-ቤት፣ የቡና-ቤት፣ የመጠጥ-ቤት፣ የምሽት-ክበብ እና ምግብ የማቅረብ ("ኬተሪንግ") አገልግሎቶች፡

**4. Investment Areas Reserved for Domestic Investors**

The following investment areas are exclusively reserved for domestic investors:

1/ Subject to applicable law, banking, insurance and microfinance businesses, excluding capital goods finance business;

2/ Transmission and distribution of electrical energy through integrated national grid system;

3/ Primary and middle level health services;

4/ Wholesale trade, petroleum ,petroleum products, wholesale of own products produced in Ethiopia; excluding wholesale of electronic commerce

5/ Retail trade, excluding retail of and electronic commerce as provided under appropriate law, of own products produced in Ethiopia;

6/ Import trade, excluding liquefied petroleum gas and bitumen;

7/ Export trade of raw coffee, khat, oil seeds, pulses, minerals, hides and skins, products of natural forest, chicken, and livestock including pack animals bought on the market;

8/ Construction and drilling services below Grade I;

9/ Hotel, lodge, resort, motel, guesthouse, and pension services, excluding those that are star-designated;

10/ Restaurant, tearoom, coffee shops, bars, nightclubs, and catering services, excluding star-designated national cuisine restaurant service;

፲፩/ የጉዞ ወኪል፣ የጉዞ ትኬት ሽያጭ እና የንግድ ድጋፊ አገልግሎቶች፡

፲፪/ የማስጎብኘት አገልግሎት፡

፲፫/ ለተወሰነ ኢንዱስትሪ የሚያገለግሉ ከባድ መሣሪያዎችን፣ ማሽኖችን እና ልዩ ተሽከርካሪዎችን ሳይጨምር መሣሪያዎች፣ ማሽኖች እና ተሽከርካሪዎች የማከራየት አገልግሎት፡

፲፬/ የሚከተሉትን መስኮች ሳይጨምር የትራንስፖርት አገልግሎት፡

ሀ) የባቡር ትራንስፖርት፡

ለ) የኬብል መኪና ትራንስፖርት፡

ሐ) የኮልድ-ቼይን ትራንስፖርት፡

መ) ከ ፳፭ ቶን በላይ የመጫን አቅም ያለው ጭነት ማጓጓዝ፣ እና

ሠ) ከመንግሥት ወይም ከአገር ውስጥ ባለሀብት ጋር በጋራ እንዲካሄዱ የተለዩ የትራንስፖርት አገልግሎቶች፡

፲፭/ አገር-በቀል ባህላዊ መድኃኒቶችን ማዘጋጀት፡

፲፮/ ለአገር ውስጥ ገበያ የሚቀርቡ የዳቦ እና የኬክ ምርቶች ማዘጋጀት፡

፲፯/ የወፍጮ ቤት አገልግሎት፡

፲፰/ የጸጉር ማስተካከል እና የቁንጅና ሳሎን አገልግሎቶች፣ የአንጥረኝነት ሥራ፣ እና በፋብሪካ ደረጃ የማይካሄድ የልብስ ስፌት፡

፲፱/ የአውሮፕላኖች ጥገና እና ዕድሳትን ጨምሮ የጥገና እና የዕድሳት አገልግሎት ሆኖም የከፍተኛ ኢንዱስትሪ ማሽነሪዎች እና የህክምና መሳሪያዎች ጥገና እና ዕድሳትን ሳይጨምር፡

፳/ በአውሮፕላን ማረፊያ ቦታ ለሚቆሙ አውሮፕላኖች የሚሰጡ እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ አገልግሎቶች፡



11/ Travel agency, travel ticket sales and trade auxiliary services;

12/ Tour operation;

13/ Operating lease of equipments, machineries and vehicles, excluding industry-specific heavy equipments, machineries and specialized vehicles;

14/ Transport services, excluding the following areas:

a) Railway transport;

b) Cable-car transport;

c) Cold-chain transport;

d) Freight transport having a capacity of more than 25 tones; and

e) Transport services reserved for joint investment with the Government or domestic investors;

15/ Making indigenous traditional medicines;

16/ Producing bakery products and pastries for domestic market;

17/ Grinding mills;

18/ Barbershop and beauty salon services, smithery, and tailoring except by garment factories;

19/ Maintenance and repair services, including aircraft maintenance repair and overhaul (MRO), but excluding repair and maintenance of heavy industry machineries and medical equipment;

20/ Aircraft ground handling and other related services.

፳፩/ እንጨት የመሰንጠቅ ሥራ፣ የጣውላ ሥራ፣ እና ያልተጠናቀቁ የእንጨት ውጤቶችን የመገጣጠም ሥራ፤

፳፪/ የመገናኛ ብዙኃን አገልግሎት፤

፳፫/ የጉምሩክ አስተላላፊነት አገልግሎት፤

፳፬/ ብሎኬት እና ጡብ ማምረት፤

፳፭/ የካባ ድንጋይ ማውጣት፤

፳፮/ የሎተሪ እና የስፖርት ውርርድ ሥራዎች፤

፳፯/ በኢንዱስትሪያል መጠን የሚከሄዱትን ሳይጨምር የልብስ ንጽህና መስጫ አገልግሎት፤

፳፰/ የትርጉም እና የጽህፈት አገልግሎቶች፤

፳፱/ የጥበቃ አገልግሎት፤

፴/ የድለላ ሥራዎች፤

፴፩/ የጥብቅና እና የሕግ ማማከር አገልግሎት፤ እና

፴፪/ ከፍተኛ የዘርፍ ዕውቀት እንዲሁም ዓለምአቀፍ ልምድ እና የሥራ ትስስር የሚጠይቁ መርከበኞችን እና ሌሎች ተመሳሳይ ሙያተኞችን ከሥራ ጋር የማገናኘት አገልግሎትን ሳይጨምር የግል ሥራ እና ሠራተኛ የማገናኘት አገልግሎት።

**፭. ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ባለሀብቶች የቅንጅት ኢንቨስትመንት የተከለሉ የኢንቨስትመንት መስኮች**

፩/ ማንኛውም የውጭ ባለሀብት በሚከተሉት የኢንቨስትመንት መስኮች ከአገር ውስጥ ባለሀብት ጋር ብቻ በቅንጅት መሠማራት ይችላል፦

ሀ) ዕቃ የማስተላለፍ እና የመርከብ ውክልና አገልግሎት፤

ለ) የአገር ውስጥ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት፤

ሐ) ከ ፵፭ በላይ መቀመጫ ባላቸው አውቶብሶች የሚሰጥ አገር-አቋራጭ የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት፤



21/ Saw milling, timber manufacturing, and assembling of semi-finished wood products;

22/ Media services;

23/ Customs clearance service;

24/ Brick and block manufacturing;

25/ Quarrying;

26/ Lottery and sports betting;

27/ Laundry services, excluding those provided on industrial scale;

28/ Translation and secretarial services;

29/ Security services;

30/ Brokerage services;

31/ Attorney and legal consultancy services; and

32/ Private employment agency services, excluding such services for the employment of seafarers and other similar professionals that require high expertise and international experience and network.

**5. Investment Areas Reserved for Joint Investment with Domestic and Foreign Investors**

1/ Any foreign investor may invest in the following investment areas only jointly with a domestic investor:

a) Freight forwarding and shipping agency services;

b) Domestic air transport service;

c) Cross-country public transport service using buses with a seating capacity of more than 45 passengers;

መ) ከፍተኛ የመጫን አቅም ያለው የከተማ ውስጥ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት፣

ሠ) የማስታወቂያ እና የፕሮሞሽን አገልግሎት፣

ረ) የድምጽ-ወምስል አገልግሎት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል እና ቪዲዮ መቅረጽ፣ ማምረት እና ማከፋፈል፣ እና

ሰ) የሂሳብ እና የኦዲት ሥራዎች።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) በተዘረዘሩት የኢንቨስትመንት መስኮች ላይ ከአገር ውስጥ ባለሀብት ጋር በቅንጅት የሚሠማራ የውጭ ባለሀብት በድርጅቱ ሊኖረው የሚችለው የካፒታል ድርሻ ከ ፵፱ በመቶ ሊበልጥ አይችልም።

## ፮. ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት የሆኑ የኢንቨስትመንት መስኮች

በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፫፣ ፬ እና ፭ ከተዘረዘሩት ውጭ ያሉ የኢንቨስትመንት መስኮች ለውጭ ባለሀብት ክፍት ናቸው።

## ክፍል ሦስት
## የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣ የነባር ድርጅት ግዢ እና በትግበራ ላይ ያለ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ማስተላለፍ

## ፯. በአገር ውስጥ ባለሀብት የሚቀርብ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ጥያቄ

ማንኛውም የአገር ውስጥ ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማግኘት ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን የጽሁፍ ወይም የኤሌክትሮኒክ ማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር አግባብነት ላለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ማቅረብ አለበት፣

፩/ ማመልከቻው የቀረበው በወኪል ከሆነ የሕጋዊ ውክልና ሥልጣን ማረጋገጫ ሰነድ ቅጂ፣

፪/ ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በግለሰብ ከሆነ የግለሰቡ የመታወቂያ ካርድ ቅጂ ወይም የአገር ውስጥ ባለሀብትነት መብት የሚያሰጥ መታወቂያ ካርድ ወይም ሌሎች ሰነዶች ቅጂ፣ እና ሁለት የቅርብ ጊዜ የፓስፖርት ፎቶ መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣



d) Urban mass transport service with large carrying capacity;

e) Advertisement and promotion services;

f) Audiovisual services; motion picture and video recording, production and distribution; and

g) Accounting and Auditing services.

2/ A foreign investor jointly investing with a domestic investor in areas listed under Sub-Article (1) of this Article shall not hold more than 49% of the share capital of the enterprise.

## 6. Investment Areas Open to Foreign Investors

Investment areas not listed under Articles 3, 4 and 5 herein are open to foreign investors.

## PART THREE
## INVESTMENT PERMIT, ACQUISITION OF EXISTING ENTERPRISE AND TRANSFER OF INVESTMENT PROJECT UNDER IMPLEMENTATION

## 7. Application for Investment Permit by a Domestic and Foreign Investor

In order to obtain investment permit, any domestic investor must fill out a paper-based or online application form and submit same to the appropriate investment organ accompanied by the following documents:

1/ Where the application is filed by an agent, a copy of valid authorization document;

2/ Where the investment is to be made by a sole proprietor, a copy of the individual's identity card or an identity card or other documents bestowing a domestic investor status, and two recent passport photo size photographs;

፫/ ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በንግድ ማህበር ከሆነ የንግድ ማህበሩ የመመሥረቻ ጽሑፍ፣ የመተዳደሪያ ደንብ እና የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ቅጂ፣ ወይም አዲስ የሚቋቋም የንግድ ማህበር ከሆነ ረቂቅ የንግድ ማህበር የመመሥረቻ ጽሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ፣ የእያንዳንዱ ማህበርተኛ መታወቂያ ካርድ ቅጂ ወይም የአገር ውስጥ ባለሀብትነት መብት የሚያሰጥ መታወቂያ ካርድ ወይም ሌሎች ሰነዶች ቅጂ፣ እና የንግድ ማህበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሁለት የቅርብ ጊዜ የፓስፖርት ፎቶ መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣

፬/ ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም በመንግሥት እና የግል ዘርፍ አጋርነት በሚቋቋም ፕሮጀክት ከሆነ ድርጅቱ ወይም የፕሮጀክት ኩባንያው የተቋቋመበት ደንብ ወይም ውሳኔ ቅጂ ወይም የመመሥረቻ ጽሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂ፣

፭/ ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በህብረት ሥራ ማህበር ከሆነ የማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂ።

፰. **በውጭ ባለሀብት የሚቀርብ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ጥያቄ**

፩/ ማንኛውም የውጭ ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማግኘት ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን የጽሁፍ ወይም የኤሌክትሮኒክ ማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት፤

ሀ) ማመልከቻው የቀረበው በወኪል ከሆነ ሕጋዊ የውክልና ሥልጣን ማረጋገጫ ሰነድ ቅጂ፣

ለ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በግለሰብ ከሆነ የግለሰቡን ማንነት የሚያረጋግጡ አግባብነት ያላቸው የጸና ፓስፖርት ገጾች ቅጂ እና ሁለት የቅርብ ጊዜ የፓስፖርት ፎቶ መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣



3/ Where the investment is to be made by a business organization, a copy of its memorandum of association and Articles of Association and commercial registration certificate; or where the business organization is to be newly established, draft memorandum of association and articles of association, a copy of each shareholder's identity card or identity card or other documents bestowing a domestic investor status, and two recent passport photo size photographs of the general manager;

4/ Where the investment is to be made by a public enterprise or project company established under public-private partnership, a copy of the regulation or decision by which it was established or a copy of its Memorandum of Association and Articles of Association;

5/ Where the investment is to be made by a cooperative society, a copy of its articles of association.

8. **Application for Investment Permit by a Foreign Investor**

1/ In order to obtain investment permit, any foreign investor must fill out a paper-based or online application form and submit same to the Commission accompanied by the following documents:

a) Where the application is filed by an agent, a copy of a valid authorization document;

b) Where the investment is to be made by a sole proprietor, a copy of bio-pages of a valid passport showing his identity and two recent passport photo size photographs;

ሐ) እንደ የውጭ ባለሀብት መቆጠር የፈለገ መደበኛ ነዋሪነቱ በውጭ አገር የሆነ ኢትዮጵያዊ ከሆነ መደበኛ የውጭ አገር ነዋሪ መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ ቅጂ እና ሁለት የቅርብ ጊዜ የፓስፖርት ፎቶ መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤

መ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው ኢትዮጵያ ውስጥ በሚቋቋም የንግድ ማህበር ከሆነ፦

(፩) ረቂቅ የንግድ ማህበሩ መመሥረቻ ጽሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ፣ የእያንዳንዱን የንግድ ማህበር አባል ማንነት የሚያረጋግጡ አግባብነት ያላቸው የጸና ፓስፖርት ገጾች ቅጂ እና የንግድ ማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ሁለት የቅርብ ጊዜ የፓስፖርት ፎቶ መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤

(፪) በንግድ ማህበሩ ውስጥ እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት መቆጠር የሚችል የውጭ ዜጋ ካለ ይህንን የሚያሳይ መታወቂያ ካርድ ወይም ሌላ አግባብነት ያለው ሰነድ ቅጂ፤

(፫) በንግድ ማህበሩ ውስጥ የንግድ ማህበር ካለ የንግድ ማህበሩ የመመሥረቻ ጽሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ወይም ተመሳሳይ የመቋቋሚያ ሰነድ ቅጂ፣ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት እና የዋና የንግድ ማህበሩ ሥልጣን ያለው አካል ኢትዮጵያ ውስጥ በኢንቨስትመንት ሥራ ለመሠማራት የወሰነበት ቃለ-ጉባኤ ቅጂ፤

ሠ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው ውጭ አገር በተቋቋመ የንግድ ማህበር የኢትዮጵያ ቅርንጫፍ ከሆነ፦



c) Where the investment is to be made by an Ethiopian national permanently residing abroad who prefers treatment as a foreign investor, a copy of document evidencing his permanent residence abroad and two recent passport photo size photographs;

d) Where the investment is to be made by a business organization to be incorporated in Ethiopia:

(1) Draft Memorandum of Association and Articles of Association of the business organization, a copy of bio-pages of a valid passport of each shareholder showing his identity, and two recent passport photo size photographs of the general manager of the business organization;

(2) Where the business organization has a foreign national member who can be considered a domestic investor, a copy of an identity card or other relevant document establishing such status;

(3) Where there is a business organization in the business organization, a copy of its Memorandum of Association and Articles of Association or similar constitutive document, commercial registration certificate and a copy of minutes of resolution passed by authorized organ of the parent business organization resolving to engage in investment activity in Ethiopia.

e) Where the investment is to be made by an Ethiopian branch of a business organization incorporated abroad:

(፩) የዋና የንግድ ማህበሩ የመመሥረቻ ጽሁፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ወይም ተመሳሳይ የመቋቋሚያ ሰነድ ቅጂ እና የንግድ ማህበሩ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ቅጂ፣

(፪) የቅርንጫፉ ሥራ አስኪያጅ የተሾመበት ሰነድ ቅጂ እና የቅርብ ጊዜ ሁለት የፓስፖርት ፎቶ መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች እንዲሁም የሥራ አስኪያጁን ማንነት የሚያረጋግጡ አግባብነት ያላቸው የጸና ፓስፖርት ገጾች ቅጂ ወይም የመታወቂያ ካርድ ቅጂ፣

(፫) የዋና የንግድ ማህበሩ ሥልጣን ያለው አካል በኢትዮጵያ ውስጥ በኢንቨስትመንት ሥራ ለመሠማራት የወሰነበት ቃለ-ጉባኤ ቅጂ፣

ረ) እንደ አስፈላጊነቱ ኮሚሽኑ ሲያምንበት የባለሀብቱን የፋይናንስ አቋም ወይም ማንነት የሚያሳይ ማስረጃ።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተጠቀሱት ምንጫቸው ከኢትዮጵያ ውጭ የሆኑ ሰነዶች ሰነዶችን የማረጋገጥ ሥልጣን ባላቸው የውጭ እና የአገር ውስጥ አካላት መረጋገጥ አለባቸው።

## ፱. ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል የሚቀርብ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ጥያቄ

ማንኛውም ባለሀብት የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ወይም ማሻሻያ ፈቃድ ለማግኘት ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን የጽሁፍ ወይም የኤሌክትሮኒክ ማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር አግባብነት ላለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ማቅረብ አለበት፦

፩/ ማመልከቻው የቀረበው በወኪል ከሆነ ሕጋዊ የውክልና ሥልጣን ማረጋገጫ ሰነድ ቅጂ፣ እና

፪/ የባለሀብቱ ወይም ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በንግድ ማህበር ከሆነ የንግድ ማህበሩ ሥራ አስኪያጅ የቅርብ ጊዜ ሁለት የፓስፖርት ፎቶ መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች።

(1) A copy of Memorandum of Association and Articles of Associations or similar constitutive document as well as commercial registration certificate of the parent business organization;

(2) A copy of document attesting appointment of the branch manager and his two recent passport photo size photographs, and a copy of bio-pages of a valid passport or identity card of the manager;

(3) A copy of minutes of resolution of the authorized organ of the parent business organization resolving to establish a branch business organization in Ethiopia;

f) Document evidencing the financial position or profile of the investor, when deemed appropriate by the Commission.

2/ Documents under Sub-Article (1) of this Article originating from outside of Ethiopia must be authenticated by foreign and domestic bodies authorized to authenticate documents.

## 9. Application for Investment Expansion or Upgrading Permit

In order to obtain investment expansion or upgrading permit, any investor must fill out a paper-based or online application form and submit same to the appropriate investment organ accompanied by the following documents:

1/ Where the application is filed by an agent, a copy of valid authorization document; and

2/ Two recent passport photo size photographs of the investor or, where the investment is made by a business organization, the general manager.

## ፲. የኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ እና አጠቃቀም

፩/ አግባብነት ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯፣ ፰ ወይም ፱ መሠረት ተሟልቶ ሲቀርብለት በባለሀብቱ ሊካሄድ የታቀደውን የኢንቨስትመንት ሥራ ከአዋጁ፣ ከዚህ ደንብ እና አግባብነት ካላቸው ሌሎች ሕጎች አንጻር በመመርመር፡

ሀ) ማመልከቻውን ከተቀበለው ወዲያውኑ ለአመልካቹ ወይም ለባለሀብቱ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፣ ወይም

ለ) ማመልከቻውን ካልተቀበለው ያልተቀበለበትን ምክንያት ጥያቄው ከቀረበበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ በሦስት (፫) የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ ወይም ለባለሀብቱ በጽሁፍ ያሳውቃል።

፪/ አግባብነት ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ከሰጠ በኋላ ለአስፈላጊው ክትትል የሚመለከታቸውን መስሪያ ቤቶች ያሳውቃል።

፫/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጠው ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቱን አጠናቆ ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት እስከሚጀምርበት ጊዜ ድረስ የንግድ ሥራ ፈቃድ እንዲያወጣ አይጠየቅም። ሆኖም፣ በአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ-አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት የኢንቨስትመንት ፈቃዱ በየአመቱ መታደስ ይኖርበታል።

፬/ አግባብነት ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት በጽሁፍ ሳይፈቅድ የኢንቨስትመንት ፈቃድን ማስተላለፍ አይቻልም።

፭/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለሌላ ሰው ሲተላለፍ ወይም በይዘቱ ላይ ሌሎች ለውጦች ሲደረጉ አግባብነት ላለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ቀርቦ መፈቀድ አለበት።

## 10. Investment Permit Issuance and Usage

1/ Upon receipt of an application made in accordance with Articles 7, 8 or 9 of this Regulation, the appropriate investment organ shall, after examining the proposed investment activity of the investor in light of the Proclamation, this Regulation and other applicable laws:

a) Where it approves the application, issue investment permit to the applicant or investor right away; or

b) Where it rejects the application, notify the applicant or investor in writing of the reason for the rejection within three (3) working days from the date following the date of application.

2/ The appropriate investment organ shall, after issuing the investment permit, notify concerned institutions for necessary follow up.

3/ A holder of an investment permit may not be required to obtain a business license until the commencement of production or rendering of service upon completion of the project. The investment permit must, however, be renewed every year as provided under Article 11 Sub-Article (1) of the Proclamation

4/ An investment permit may not be transferred without prior written approval of the appropriate investment organ.

5/ Where an investment permit is transferred to another person or where any change is made to its content; it shall be submitted to the appropriate investment organ for approval.

## ፲፩. የነባር ድርጅት ግዢ

፩/ ነባር ድርጅትን ወይም የነባር ድርጅትን አክሲዮን ለመግዛት የሚፈልግ የውጭ ባለሀብት ጥያቄውን ለኮሚሽኑ በጽሑፍ ወይም ኤሌክትሮኒክ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት።

፪/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርብለትን ጥያቄ ሲመለከት ባለሀብቱ የሚገዛው ነባር ድርጅት ወይም አክሲዮን ገዝቶ አባል የሚሆንበት ማህበር የተሠማራበት የኢንቨስትመንት መስክ ለውጭ ባለሀብት ያልተከለከለ መሆኑን፤ እንዲሁም በአዋጁ የተመለከተው የዝቅተኛ ካፒታል መጠን ግዴታ እና በንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተመለከቱ ግዴታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡ የነባር ድርጅትን ወይም የነባር ድርጅትን አክስዮን ለመግዛት የሚያመለክት የውጭ ባለሀብት ከንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እንዲሁም ከገቢዎች ሚኒስቴር አስፈላጊውን ክሊራንስ ማቅረብ ይኖርበታል።

፬/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት ማመልከቻውን በመመርመር፡

ሀ) ማመልከቻውን ከተቀበለው የንግድ ሥራ ፈቃዱን ወዲያውኑ ይተካል ወይም የአክሲዮን ዝውውሩን ይመዘግባል፡ ወይም

ለ) ጥያቄውን ካልተቀበለው ያልተቀበለበትን ምክንያት ለባለሀብቱ ጥያቄው ከቀረበበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ በሦስት (፫) የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ያሳውቃል።



## 11. Acquisition of Existing Enterprise

1/ A foreign investor seeking to buy an existing enterprise or a share thereof must submit a paper-based or online application to the Commission.

2/ The Commission, in reviewing an application filed in accordance with Sub-Article (1) of this Article, must ascertain that the enterprise is engaged in investment areas open to foreign investors, and that the minimum capital requirement provided in the Proclamation and other requirements laid down under the Commercial Registration and Business Licensing Proclamation and other applicable laws are met.

3/ Subject to the provision of Sub-Article (2) of this Article, a foreign investor applying to buy an existing enterprise or a share thereof must adduce the necessary clearance from the Ministry of Trade and Industry and the Ministry of Revenues.

4/ The Commission shall, after examining the request in accordance with Sub-Articles (2) and (3) of this Article:

a) Where it approves the application, replace the business license or register the share transfer right away; or

b) Where it rejects the application, notify the investor in writing of the reason for the rejection within three (3) working days from the date following the date of application.

**፲፪. በትግበራ ላይ የሚገኝ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ማስተላለፍ**

፩/ የንግድ ሥራ ፈቃድ ከማውጣቱ በፊት በትግበራ ላይ የሚገኝ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቱን ለሌላ ባለሀብት ማስተላለፍ የሚፈልግ ማንኛውም ባለሀብት ጥያቄውን አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ ማመልከቻ በማቅረብ ማስፈቀድ አለበት።

፪/ ባለሀብቱ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቱን ለማስተላለፍ ከሚያቀርበው ማመልከቻ ጋር የሚከተሉትን ሰነዶች አያይዞ ማቅረብ አለበት:

ሀ) የታደሰ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ቅጂ፡

ለ) ሰነዶችን የመመዝገብ እና የማረጋገጥ ሥልጣን ባለው አካል የተመዘገበ የሽያጭ ስምምነት ቅጂ፡

ሐ) ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ በሊዝ የተረከበው መሬት ካለ መሬቱ ለገዢው የተላለፈበት ሰነድ ቅጂ።

፫/ አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት የቀረበውን ማመልከቻ በመመርመር:

ሀ) ማመልከቻውን ከተቀበለ የፕሮጀክት ማስተላለፉን ወዲያውኑ ይፈቅዳል፡

ለ) ማመልከቻውን ካልተቀበለው ያልተቀበለበትን ምክንያት ለባለሀብቱ ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ በሦስት (፫) የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ያሳውቃል።

**12. Transfer of Investment Project Under Implementation**

1/ Any investor who wishes to transfer to another investor an investment project under implementation for which a business license is not yet issued must obtain the approval of the appropriate investment organ by submitting a paper-based or online application.

2/ The investor shall, together with application for approval of the transfer of an investment project, submit the following documents:

a) A copy of renewed investment permit;

b) A copy of sale agreement registered with notary public; and

c) Where land was received for the project, a copy of document showing that the land is transferred to the buyer.

3/ The appropriate investment organ, after examining the application, shall:

a) Where it accepts the application, approve the project transfer right away;

b) Where it rejects the application, notify the investor in writing of its decision for the rejection within three (3) working days from the date following the date of application.

## ክፍል አራት

## የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሚታገድበት እና የሚሰረዝበት ሥርዓት

### ፲፫.የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሚታገድበት ሥርዓት

፩/ ማንኛውም ባለሀብት በአዋጁ አንቀጽ ፲፫ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተመለከተ ማናቸውንም ጥሰት መፈጸሙ ከታመነ ከ ፷ (ስልሳ) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ ወይም ተቀባይነት ያለው ምላሽ እንዲያቀርብ አግባብነት ባለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት ማስጠንቀቂያ የደረሰው ባለሀብት የሚጠበቀውን ማስተካከያ ካላደረገ ወይም ለማስጠንቀቂያው ተቀባይነት ያለው ምላሽ ካልሰጠ አግባብነት ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት በአዋጁ አንቀጽ ፲፫ ንዑስ-አንቀጽ (፪) ለተደነገገው ጊዜ የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ሊያግድ ይችላል።

### ፲፬. የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሚሰረዝበት ሥርዓት

፩/ አግባብነት ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት በአዋጁ አንቀጽ ፲፫ ንዑስ-አንቀጽ (፫) በተመለከቱት ምክንያቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከመሰረዙ በፊት የስረዛ እርምጃውን የሚወስድበትን ምክንያት ለባለሀብቱ በጽሁፍ ያሳውቃል፡ ባለሀብቱ በጉዳዩ ላይ ያለውን አስተያየት በ፲፭ (አስራ አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት ማስታወቂያ የደረሰው ባለሀብት ምላሽ ካልሰጠ ወይም የሰጠው መልስ ተቀባይነት የሌለው ከሆነ አግባብነት ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ሊሰርዝ ይችላል።



## PART FOUR

## PROCEDURES FOR SUSPENSION AND REVOCATION OF INVESTMENT PERMIT

### 13. Procedure for Suspension of Investment Permit

1/ Where it is believed that an investor has committed any of the violations stated under Article 13 Sub-Article (1) of the Proclamation, he shall be given a written warning notice by the appropriate investment organ to take the necessary corrective measures or furnish adequate response within a period not exceeding 60 (sixty) working days.

2/ Where an investor who has received a warning notice under Sub-Article (1) of this Article fails to take the required corrective measure or to submit adequate response, the appropriate investment organ may suspend the investment permit for the period provided in Article 13 Sub-ar icle (2) of the Proclamation.

### 14. Procedure for Revocation of Investment Permit

1/ Before revoking an investment permit on the basis of grounds specified under Article 13 Sub-Article (3) of the Proclamation, the appropriate investment organ shall notify the investor in writing of the reasons for the impending revocation measure; the investor shall submit his written statement within 15 (fifteen) working days.

2/ The appropriate investment organ may revoke the investment permit where the investor who received notification as per Sub-Article (1) of this Article fails to respond or the response he provided is not found acceptable.

## ክፍል አምስት
## የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የትብብር ስምምነቶች ምዝገባ

### ፲፭. የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፭ መሠረት የሚቀርብ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት ምዝገባ ጥያቄ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡

ሀ) በቴክኖሎጂ ተቀባዩ የተፈረመ የማመልከቻ ቅጽ፡

ለ) በቴክኖሎጂ ተቀባይ እና አቅራቢው መካከል የተደረገ ሰነዶችን የመመዝገብ እና የማረጋገጥ ሥልጣን ባለው አካል የተመዘገበ ስምምነት ቅጂ፡

ሐ) የቴክኖሎጂ ተቀባዩ የጸና የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ቅጂ፡ እና

መ) የቴክኖሎጂ አቅራቢው የንግድ ምዝገባ ወይም የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም የቴክኖሎጂ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ቅጂ።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተጠቀሱት ምንጫቸው ከኢትዮጵያ ውጭ የሆኑ ሰነዶች ሰነዶችን የማረጋገጥ ሥልጣን ባላቸው የውጭ እና የአገር ውስጥ አካላት መረጋገጥ አለባቸው።

፫/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የምዝገባ ማመልከቻ ተሟልቶ ሲቀርብለት አስፈላጊውን ግምገማ በማድረግ በ፴ (ሰላሳ) የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

፬/ ኮሚሽኑ የስምምነት ምዝገባ ጥያቄን ከተቀበለ ስምምነቱን በመመዝገብ የምዝገባ ማስረጃ ለአመልካቹ ይሰጣል፡ ጥያቄውን ካልተቀበለ ውሳኔውን በጽሁፍ ለአመልካቹ ያሳውቃል።

## PART FIVE
## REGISTRATION OF TECHNOLOGY TRANSFER AND COLLABORATION AGREEMENTS

### 15. Technology Transfer Agreement

1/ A technology transfer agreement registration request made pursuant to Article 15 of the Proclamation shall be accompanied by the following:

a) An application form signed by the technology recipient;

b) A copy of technology transfer agreement concluded between the recipient and technology provider and registered with notary public;

c) A copy of valid business license or investment permit of the technology recipient; and

d) A copy of the commercial registration certificate or business license or document ascertaining ownership of technology of the technology provider.

2/ Documents under Sub-Article (1) of this Article originating from outside of Ethiopia must be authenticated by foreign and domestic bodies authorized to authenticate documents.

3/ Upon receipt of a complete application for registration in accordance with Sub Article -article (1) of this Article, the Commission shall pass a decision within 30 (thirty) working days having conducted the necessary review.

4/ Where the Commission approve the request, it shall register the agreement and issue a certificate of registration to the applicant; where it rejects the application, it shall notify the applicant of its decision in writing.

፭/ ኮሚሽኑ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት ተገቢነት የሚወሰንበት፡ ለቴክኖሎጂ ይዘት ግምገማ ዓላማ ሲባል ልዩ የዘርፍ ዕውቀት ካላቸው ተቋማት ጋር የሚኖረው ቅንጅታዊ አሠራር የሚመራበት፡ እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ ለቴክኖሎጂ ተቀባይ የመረጃ ድጋፍ ሊሰጥ የሚቻልበት ሁኔታን የሚወስን ዝርዝር የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል።

## ፲፮. ከወጭ ንግድ ጋር በተያያዘ የውጭ ድርጅት የካፒታል መዋጮ ሳይኖረው የሚያደርገው ትብብር

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፮ መሠረት የሚቀርብ የትብብር ስምምነት ምዝገባ ጥያቄ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

ሀ) በአገር ውስጥ ባለሀብት የተፈረመ ማመልከቻ ቅጽ፡

ለ) በአገር ውስጥ ባለሀብቱ እና በውጭ ኢንተርፕራይዝ መካከል የተደረገ ሰነዶችን የመመዝገብ እና የማረጋገጥ ሥልጣን ባለው አካል የተመዘገበ የትብብር ስምምነት ሰነድ ቅጂ፡

ሐ) የአገር ውስጥ ባለሀብቱ የጸና የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ቅጂ፡ እና

መ) የውጭ ኢንተርፕራይዙ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም የንግድ ሥራ ፈቃድ ቅጂ።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተጠቀሱት ምንጫቸው ከኢትዮጵያ ውጭ የሆኑ ሰነዶች ሰነዶችን የማረጋገጥ ሥልጣን ባላቸው የውጭ እና የአገር ውስጥ አካላት መረጋገጥ አለባቸው።



5/ The Commission shall establish detailed guideline for determining the appropriateness of technology transfer agreement, for managing collaboration with institutions having sectoral-expertise for the purpose of assessing technology content, and, as necessary, for determining the conditions under which informational support may be provided to technology recipients.

## 16. Export-Oriented None-Equity-Based Foreign Enterprise Collaboration

1/ A collaboration agreement registration request made pursuant to Article 16 of the Proclamation shall be accompanied by the following:

a) An application form signed by a domestic investor;

b) A copy of a collaboration agreement between the domestic investor and a foreign enterprise registered with notary public;

c) A copy of a valid business license or investment permit of the domestic investor; and

d) A copy of the commercial registration certificate or business license of the foreign enterprise.

2/ Documents under Sub-Article (1) of this Article originating from outside of Ethiopia must be authenticated by foreign and domestic bodies authorized to authenticate documents.

፫/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የምዝገባ ማመልከቻ ተሟልቶ ሲቀርብለት አስፈላጊውን ግምገማ በማድረግ በ፴ (ሰላሳ) የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

፬/ ኮሚሽኑ የቀረበውን የስምምነት ምዝገባ ጥያቄ ከተቀበለ ስምምነቱን በመመዝገብ የምዝገባ ማስረጃ ለአገር ውስጥ ባለሀብቱ ይሰጣል፡ ጥያቄውን ካልተቀበለ ውሳኔውን ለአገር ውስጥ ባለሀብቱ በጽሁፍ ያሳውቃል።

## ክፍል ስድስት

## የመኖሪያ ቤት ባለቤት መሆን የሚቻልበት ሁኔታ፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ

### ፲፯. የመኖሪያ ቤት ባለቤት መሆን የሚቻልበት ሁኔታ

የውጭ ባለሀብት ወይም እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት የተቆጠረ የውጭ ዜጋ በአዋጁ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ-አንቀጽ (፪) መሠረት የመኖሪያ ቤት ባለቤት መሆን የሚችለው ቢያንስ ፲ ሚሊዮን (አስር ሚሊዮን) የአሜሪካን ዶላር በሥራ ላይ ያዋለ ከሆነ ነው።

### ፲፰.የአንድ ማዕከል አገልግሎት

፩/ አግባብነት ባላቸው የኢንዱስትሪ ፓርክ ሕጎች በፓርክ ደረጃ ወይም ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ውጭ ባሉ የአገልግሎት መስጫዎች የሚሰጡ የአንድ ማዕከል አሠራሮች እንደተጠበቁ ሆኖ፡ ኮሚሽኑ የውጭ ቀጥተኛ ካፒታል ይመዘግባል፡ የሚመለከታቸው የመንግሥት አስፈጻሚ አካላትን በመወከል የሚከተሉትን አገልግሎቶች ይሰጣል፡



3/ Upon receipt of a complete application for registration in accordance with Sub-Article (1) of this Article, the Commission shall render decision within 30 (thirty) working days having conducted the necessary review.

4/ Where the Commission approve the request, it shall register the agreement and issue a certificate of registration to the domestic investor; where it rejects the application, it shall notify the domestic investor of its decision in writing.

## PART SIX

## CONDITION FOR OWNING A DWELLING HOUSE; PROVISION OF ONE-STOP SERVICE

### 17. Condition for Owning a Dwelling House

A foreign investor or a foreign national treated as a domestic investor may own a dwelling house as per Article 18 Sub-Article (2) of the Proclamation if he has invested a minimum of USD 10,000,000.00 (Ten Million)

### 18. One-Stop-Service

1/ Without prejudice to one-stop services provided in industrial parks or other service provision locations pursuant to industrial park laws, the Commission shall register foreign direct capital and provide the following services representing the relevant Government executive organs:

ሀ) የመመሥረቻ ጽሁፎች እና የመተዳደሪያ ደንቦች እንዲሁም ማሻሻያዎችን መመዝገብ፣

ለ) የንግድ ወይም የማህበር ስም መመዝገብ፣ ማሻሻል፣ መተካት፣ መሰረዝ፣

ሐ) በንግድ መዝገብ ውስጥ ማስገባት እና የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት መስጠት፣ ማሻሻል፣ መተካት፣ መሰረዝ፣

መ) ለውጭ ዜጋ ተቀጣሪዎች የሥራ ፈቃድ መስጠት፣ ማደስ፣ መተካት፣ ፈቃዱን ማገድ፣ መሰረዝ፣

ሠ) የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጠት፣ ማደስ፣ ማገድ፣ ምትክ መስጠት እና መሰረዝ፣ እና

ረ) የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ጥያቄዎችን አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ማስተናገድ፣ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የቀረጥ ነጻ መብት ካለው አንድ ባለሀብት ወደ ሌላ የቀረጥ ነጻ መብት ያለው ባለሀብት የግንባታ ዕቃዎች፣ የካፒታል ዕቃዎች፣ የመለዋወጫ ዕቃዎች እና ተሽከርካሪዎች የማስተላለፍ ጥያቄዎችን ማስተናገድ።

፪/ የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሠ) መሠረት የሚከናወን የንግድ ሥራ ፈቃድ ዕድሳት በሕግ አግባብ መፈጸሙን ይከታተላል።

፫/ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት በኮሚሽኑ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ዴስክ በማቋቋም የሚከተሉትን አገልግሎቶች ይሰጣሉ።



a) Registration of Memorandum of Association, Articles of Association, and amendments thereto;

b) Registration, amendment, replacement, and cancellation of trade names and business names;

c) Registration in commercial register and issuance, amendment, replacement and cancellation of commercial registration certificate;

d) Issuance, renewal, replacement, suspension and cancellation of expat work permits;

e) Issuance, renewal, suspension, replacement and revocation of business license; and

f) Handling of investment incentive requests in accordance with the applicable law; handling of requests for the transfer of construction materials, capital goods, spare parts and vehicles from one investor having duty-free right to another investor having the same right in accordance with the applicable law

2/ The Ministry of Trade and Industry shall follow up that the renewal of business license as per Sub-Article (1) paragraph (e) of this Article is carried out in accordance with the law.

3/ The pertinent Government Agencies shall set up desks and provide the following services at the Commission's one stop shop:

ሀ) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መስጠት፡

ለ) የመኖሪያ ፈቃድ መስጠት፡

ሐ) የግንባታ ፈቃድ መስጠት፡ እና

መ)የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት አጽድቆ የምስክር ወረቀት መስጠት።

፫/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) እና (፫) ከተመለከቱት ውጭ በአንድ ማዕከል አሠራር ተጨማሪ አገልግሎቶች እንዲሰጡ ሊወስን ይችላል።

፬/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩ አገልግሎቶችን አስመልክቶ ጥያቄ ሲቀርብለት ማመልከቻው ተሟልቶ የቀረበ መሆኑን በማረጋገጥ እና ጉዳዩን አግባብ ካለው ሕግ አንጻር በመመርመር፡

ሀ) ማመልከቻውን ከተቀበለው ተገቢውን ክፍያ በማስከፈል የተጠየቀውን አገልግሎት ይሰጣል፣ ለአስፈላጊው ክትትልም የሰጠውን አገልግሎት ወይም ማስረጃ አግባብነት ላላቸው የመንግሥት አካላት ያሳውቃል፡ ወይም

ለ) ማመልከቻውን ካልተቀበለው ያልተቀበለበትን ምክንያት ለባለሀብቱ ወይም ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቃል።



a) Issuance of tax identification number;

b) Issuance of residence permit;

c) Issuance of construction permit; and

d) Approval of environmental impact assessment studies and issuance of certificate;

3/ When necessary, the Commission may determine to provide additional one-stop services supplementing the list under Sub-Articles (1) and (3) of this Article.

4/ Upon receipt of application for services provided under Sub-Article (1) of this Article, the Commission, having ascertained completeness of the application and reviewed it pursuant to the applicable law, shall:

a) Where it approves the application, provide the service requested by charging the proper fee, and notify relevant Government organs of the service provided or accreditation issued for necessary follow-up; or

b) Where it rejects the application, notify the investor or applicant in writing of the reason for the rejection.

፭/ ባለሀብቶች ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶቻቸው የሚያስፈልግ መሬት፣ ብድር፣ የውሃ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል እና የቴሌኮም አገልግሎቶች፣ እንዲሁም ለራሳቸው እና ለሚቀጥሯቸው የውጭ አገር ዜጎች ቪዛ እና የመኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት ለሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች አግባብነት ያላቸው የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣሉ። ለዚህ ድንጋጌ አፈጻጸም የሚመለከታቸው የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳድር ተቋማት የባለሀብቶችን ጥያቄ በቅልጥፍና የሚያስተናግዱ የኢንቨስትመንት ዴስኮችን ማቋቋም አለባቸው።

## ክፍል ሰባት

## ለኢትዮጵያውያን ሠራተኞች የሚሰጥ ሥልጠና እና የሚደረግ የዕውቀት እና ክህሎት ሽግግር

### ፲፱. ለኢትዮጵያውያን ሠራተኞች የሚሰጥ ሥልጠና እና የዕውቀት እና ክህሎት ሽግግር አሠራር

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት ቀጣይነት ባለው የሙያ መስክ የውጭ አገር ዜጎችን የሚቀጥር ባለሀብት በግልጽ በተወሰነ የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ ለኢትዮጵያውያን አስፈላጊውን የሥራ ላይ ሥልጠና እንዲሰጥ እና ዕውቀት እንዲተላለፍ በማድረግ የውጭ ዜጋ ተቀጣሪዎች በኢትዮጵያውያን እንዲተኩ የማድረግ ግዴታ አለበት።

፪/ ባለሀብቱ የንግድ ሥራ ፈቃድ በተሰጠው በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ የሥልጠናውን ዓይነት እና መርሀ-ግብር የሚያሳይ መግለጫ፣ ይህን ተከትሎም የመርሀ-ግብሩን የየሩብ አመት የአፈጻጸም ሪፖርት ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) መሠረት የሚቀርበው ሪፖርት የሚከተሉትን ዝርዝሮች የያዘ መሆን አለበት፦

5/ The appropriate investment organs shall provide support to requests of investors in respect of their investments to obtain land, loan, water, electric power, telecom services, as well as visa and residence permits for themselves and their expat employees. For the implementation of this provision, relevant organs of the Federal Government and Regional State Administrations must establish investment help desks that handle investors' requests expeditiously.

## PART SEVEN

## TRAINING AND TRANSFER OF KNOWLEDGE AND SKILL TO ETHIOPIAN EMPLOYEES

### 19. Procedure for the Training of and Transfer of Knowledge and Skill to Ethiopian Employees

1/ An investor employing foreigners in permanent fields of occupation pursuant to Article 22 Sub-Article (1) of the Proclamation is obliged to replace expat employees by Ethiopians within a clearly set timeframe by providing the needed on-the-job training and facilitating the transfer of knowledge.

2/ The investor must, within three months of the issuance of business license, submit to the Commission a statement detailing the type and schedule of the training, and, thereafter, a quarterly implementation report of the training program.

3/ The report submitted pursuant to Sub-Article (2) of this Article shall contain the following details:

ሀ) የውጭ አገር ዜጋው ሙሉ ስም እና የተቀጠረበት የሙያ መስክ፣

ለ) የሥራ-ላይ ሥልጠና የሚሰጣቸው ኢትዮጵያውያን ሙሉ ስም እና አድራሻ፣

ሐ) የሚሰጠው የሥራ-ላይ ሥልጠና ዓይነት እና የሚወስደው ጊዜ፣ እና

መ) በተተኪነት የሚታሰቡት ኢትዮጵያውያን ሰልጣኞች ተገቢውን ዕውቀት እና ችሎታ በሚፈለገው መጠን እና ጊዜ እየቀሰሙ ያልሆነ እንደሆነ ለዚህ ማብራሪያ።

፬/ ኮሚሽኑ ከንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ከሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በዚህ አንቀጽ እና በአዋጁ አንቀጽ ፳፪ የተደነገጉ ጉዳዮችን የሚመለከት የአሠራር መመሪያ ያዘጋጃል፣ ተፈጻሚም ያደርጋል።

## ክፍል ስምንት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳. የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

፩/ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች እና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለሉ የሥራ መስኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፸/፪ሺ፬ (እንደተሻሻለ) የኢንቨስትመንት (የሥራ) መስኮችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በዚህ ደንብ ተሽረዋል።

፪/ ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ ደንብ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

a) The full name of the foreign national and the occupational field in which he is hired;

b) The full name and address of Ethiopians receiving the on-the-job training;

c) The type of training offered and the duration for which the training lasts;

d) Where Ethiopian trainees are not acquiring the necessary knowledge and skill to the extent and within the time desired an explanation thereon.

4/ In collaboration with the Ministry of Trade and Industry and the Ministry of Labour and Social Affairs, the Commission shall prepare and implement a working guideline regulating matters specified under this Article and Article 22 of the Proclamation.

## PART EIGHT
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 20. Repealed and Inapplicable Laws

1/ The Provisions on investment areas in the Investment Incentives and Investment Areas Reserved for Domestic Investors Council of Ministers Regulation No. 270/2012 (as amended) are hereby repealed.

2/ No Regulation, Directive or Customary practice shall, in so far as it is inconsistent with this Regulation, be applicable with respect to matters provided for in this Regulation.

፳፩.<u>ተፈጻሚነታቸው የሚቀጥል ድንጋጌዎች</u>

የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች እና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለሉ የሥራ መስኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፸/፪ሺ፲፪ (እንደተሻሻለ) የኢንቨስትመንት ማበረታቻን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በሌላ ሕግ እስኪሻሩ ድረስ እንደጸኑ ይቆያሉ።

፳፪.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም.**

**ዐብይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

21. <u>**Unrepealed Provisions**</u>

The provisions of the Investment Incentives and Investment Areas Reserved for Domestic Investors Council of Ministers Regulation No. 270/2012 (as amended) relating to investment incentives shall remain valid until they are repealed by another law.

22. <u>**Effective Date**</u>

This Regulation shall come into force on the date of publication in Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa On the 2nd Day of September 2020.**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINSTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**